


“ጌታ ከፍተኛ ፈውስና እጅግ በጣም ታላቅ መሣሪያ አድርጎ
ለመላው ዓለም መፈወሻ ያዘዘው የሕዝቦችዋን በአንድ ዓለም ዓቀፋዊ
ዓላማ÷ በአንድ የጋራ እምነት ሥር መሰባሰብ ነው::”

Ann's A5 texts.indd 1 2/3/2008 4:11:23 AM

# መግቢያ

የባሃኢ ሃይማኖት ዓለም አቀፋዊ ሲሆን ዓላማውም ሁሉንም ዘሮችና ሕዝቦች በአንድ ሁሉን አቀፍ እቅድና ሃይማኖት ለማዋሃድ ነው::

ባሃኦላህ የባሃኢ ሃይማኖት መስራች ሲሆን ተከታዮቹም ባሃኢዎች ይባላሉ:: ባሃኦላህ እንደሚመጣ በሁሉም ሃይማኖቶች ቅዱሳን ጽሑፎች ቃል የተገባለት ነው ብለን እናምናለን:: ሰላምና ስምምነት በምድር ላይ ይመሰረታል፤ የሰው ልጆችም በታላቅ ፍስሃ ይኖራሉ የሚለው ቃል-ኪዳን ይሟላ ዘንድ ባሃኦላህ ከአምላክ ትምህርቶችና መመሪያዎችን ይዞልን መጥቷል:: በጽሑፎቹም ባሃኦላህ እንዲህ ይላል:-

“ጌታ ከፍተኛ ፈውስና እጅግ በጣም ታላቅ መሣሪያ አድርጎ ለመላው ዓለም መፈወሻ ያዘዘው የሕዝቦችዋን በአንድ ዓለም ዓቀፋዊ ዓላማ÷ በአንድ የጋራ እምነት ሥር መሰባሰብ ነው::”

# እግዚአብሔር

የእግዚአብሔር ሕላዌ የማይታወቅ መሆኑን ባሃኦላህ ያስተምረናል:: ይህ ማለት እኛ አዋቂና ብልህ ብንሆንም እንኳ የአምላክን ተፈጥሮ ማወቅ አይቻለንም:: አንድ ጠረጴዛ የሰራውን አናጢ ተፈጥሮ መገንዘብ አይቻለውም:: በተመሳሳይ ሁናቴ እኛ ሰዎች የፈጠረንን ፈጣሪያችንን መገንዘብ አንችልም::

እግዚአብሔር የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ ነው:: ሰማያትንና ምድርንም ከነተራሮቿና ሸለቆዎቿ÷ በረሃዎቿና ባህሮቿ÷ ወንዞቿ መስኮቿና ዛፎቿ ጋር ፈጠረ:: እግዚአብሔር እንስሳትንና ሰውን ፈጠረ:: ባሃኦላህ እንደሚነግረን የመፈጠራችን ምክንያት ፍቅር ነው::

“የሰው ልጅ ሆይ!
ያንተን መፈጠር ወደድሁ÷ ስለዚህም ፈጠርሁህ:: ... ስምህን እንዳነሳና ነፍስህን በሕይወት እስትንፋስ እሞላት ዘንድ አንተም አፍቅረኝ::”

# ቃል-ኪዳን

ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ሐሳቡ ከግንዛቤያችን ውጭ ቢሆንም ፍቅሩ ሕይወታችንንና ሕልውናችንን ሳያቋርጥ ይዳስሳል። ይህ ፍቅር ወደ እኛ የሚደርሰው በዘለአለማዊው ቃል-ኪዳኑ አማካይነት ነው። በዚህ ዘለአለማዊ ቃል-ኪዳን መሠረት እግዚአብሔር ብቻችንንና ያለመመሪያ ፈጽሞ አይተወንም። የሰው ልጅ ከእርሱ በራቀና ትምህርቶቹን በረሳ ቁጥር እግዚአብሔር ክስተቱን ይልክና ፈቃዱንና ዓላማውን ያሳውቀናል።

# ግልጸቶች

“ግልጸት” የሚለው ቃል ከዚህ በፊት የማይታወቅን ነገር ማሳወቅ ማለት ነው:: የእግዚአብሔር ግልጸቶች የእግዚአብሔርን ቃልና ፈቃድ ለሰው ልጅ የሚገልጹ ፍጹም የሆኑ ስብዕናዎች ናቸው:: ስለሆነም እነርሱን ካዳመጥን ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ ሰጠን ማለት ነው:: ከዚህ በፊት ከነበሩት ግልጸቶች መካከል አብርሃም÷ ሙሴ ÷ ጌታ እየሱስ እና ነብዩ ሙሐመድ ይገኙበታል:: እኛ ላለንበት ዘመን የተላከው ግልጸት ደግሞ ባሃኦላህ ነው::

“ግልጸት” የሚለውን ጽንሰ-ሃሳብ ለመገንዘብ የሚረዳንን ምሳሌ እንመልከት:: በዚህ ዓለም ፀሐይ የሙቀትና የብርሃን ሁሉ ምንጭ ናት:: ያለሙቀትና ብርሃን በምድራችን ላይ ምንም ሕይወት ሊኖር አይችልም:: ሆኖም ፀሐይ ወደ መሬት አትወርድም፤ እኛም ፀሐይን ለመቅረብ ብንሞክር ሙሉ ለሙሉ እንቀልጣለን:: ነገር ግን የተወለወለ መስታወትን ወስደን ወደ ፀሐይ አዞርነው እንበል:: በመስታወቱ ውስጥ የፀሐይን ምስል እናያለን:: መስታወቱ በደንብ ከተወለወለ ምስሉ የበለጠ ፍፁም ይሆናል:: የእግዚአብሔር ግልጸቶች የእግዚአብሔርን ብርሃን በምልዐተ-ጸዳሉ የሚያንፀባርቁ ፍፁም ንጹሕ የሆኑ መስታዎት ናቸው:: እነኝህ መስታዎት ማለትም ሁሉም ግልጸቶች የሚያንጸባርቁት አንድ የሆነውን የእግዚአብሔርን ብርሃን ነው:: እግዚአብሔርን ልንደርስበት አንችልም እነኚህ ፍፁም ስብዕናዎች ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ እኛ ይመጣሉ÷ በመካከላችን ይኖራሉ መመሪያም ይሰጡናል÷ ቁሳዊና መንፈሣዊ ዕድገት ለመቀዳጀት በሚያስፈልገን ኃይል ይሞሉናል::

# ባሃኦላህ - የዘመኑ ግልጸት

ሁሉም መስታዎቶች የተለያዩ ሊመስሉ ይችላሉ። ነገር ግን ሁሉም ከፀሐይ የሚመጣውን ብርሃን ለማንፀባረቅ እኩል እምቅ ኃይል አላቸው። እንዲሁም ሁሉም የእግዚአብሔር ግልጸቶች በተለያየ ሁኔታ÷ማዕረግና ክብር ምድር ላይ ይከሰታሉ።

ስለዚህ የባሃኦላህ ትምህርቶች ከሁሉም ክስተቶች ትምህርቶች ጋር ፍፁም ይስማማሉ። በተጨማሪም የዘመናችንን የሰው ልጅ ሁኔታ የሚመለከቱ ናቸው። የዘመናችንን የሰውን ልጅ ሁኔታ በትኩረት ብንመለከት የእግዚአብሐር ግልጸት መምጣት ያለበት ትክክለኛው ጊዜ አሁን መሆኑን እንገነዘባለን። ስለምንኖርበት ዘመን ባሃኦላህ ሲናገር፡-

“ይህ ቀን የእግዚአብሔር እጅግ በጣም የላቁ ችሮታዎች በሰዎች ላይ የፈሰሱበት÷ የእርሱ እጅግ በጣም ታላቅ ፀጋ በተፈጠሩት ነገሮች ውስጥ የተናኘበት÷ ቀን ነው። የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ልዩነታቸውን በማስወገድ በእርሱ እንክብካቤ ፍቅራዊ ደግነት ዛፍ ጥላ ሥር በፍጹም አንድነትና ሰላም መኖር አለባቸው።”

# የሰው ዘር አንድነት

የባሃኢ ሃይማኖት ዓላማ የሰው ዘር አንድነትን መመሥረት ነው። እኛ ሁላችንም የአንድ ዛፍ ፍሬዎችና የአንድ ቅርንጫፍ ቅጠሎች መሆናችንን ባሃኦላህ ያስተምረናል። ምንም እንኳን የተለያየ ዘር፥ ቀለምና ብሔር ቢኖረንም ሥረ መሠረታችን ግን አንድ ነው። ሁላችንም የሰው ዘር ቤተሰብ አባላት ነን።

የሰው ዘር በአንድ ሰፊ የአትክልት ስፍራ ሊመሰል ይችላል። በዚህ አትክልት ስፍራ የተለያዩ ቅርፆች ቀለሞችና መዓዛዎች ያሏቸው አበባዎች ጎን ለጎን ያድጋሉ። የአትክልት ሥፍራው ውበት የአበቦቹ የተለያየ ቀለም ቅርጽና መዓዛ ውጤት ነው። ልክ እንደዚሁ የሰው ዘርን ሁሉ በአትክልት ቦታ እንደሚበቅሉ የተለያዩ ውብ አበቦች አድርገን ማየት አለብን። በአካላዊ አቋማችን፥ በባሕሪያችን፥ ከተለያዩ ማህበረሰቦችና ሃይማኖቶች በመምጣታችን፥ በሃሳባችንና በአስተሳሰቦቻችን መካከል ያሉት ልዩነቶች ግጭትንና ጥልን እንዲያመጡ መፍቀድ የለብንም። አንድ ሰው የባሃኢ ማህበረሰብን ለመቀላቀል ምርጫው ቢሆን ባሃኢዎች አንድነትን ለመገንባትና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ በምናደርገው ጥረት ተሳታፊ ይሆናል።

ከከንቱ ጥላቻ ነጻ ለመሆን የተቻለንን ሁሉ ማድረግ አለብን፦ “የጦርነት ሃሳብ ሲመጣ ይበልጥ ጠንካራ በሆነው በሰላም ሃሳብ ተቃወሙት። የጥላቻ ሃሳብ ይበልጥ ኃይለኛ በሆነው በፍቅር ሃሳብ መደምሰስ አለበት።”

# የባሃኦላህ ሕይወት

ባሃኦላህ በኢራን አገር ዋና ከተማ በቴህራን እ.ኤ.አ በ1817 ተወለደ:: ከልጅነቱ ጀምሮ የታላቅነት ምልክቶች ይታዩበት ነበር:: ትምህርት ቤት መግባት አላስፈለገውም ነበር ምክንያቱም ዕውቀትን ሁሉ እግዚአብሔር ሰጥቶት ስለነበር ነው:: ባሃኦላህ ታላቅና ታዋቂ ከሆነ ቤተሰብ ነበር የተወለደው:: ወጣት በነበረበት ጊዜ ንጉሡ ከፍተኛ ሹመት ሰጥቶት ነበር:: እርሱ ግን አልተቀበለውም:: ጊዜውን የተጨቆኑትን÷ሕሙማንና ድሆችን በመርዳት እንዲሁም ፍትህን በማራመድ ሊያውለው ፈለገ::

Ann's A5 texts.indd 8 2/3/2008 4:11:24 AM

# የባሃኦላህ መከራ

በተለይ ልገልጽላችሁ የምፈልገው ሁለት የባሃኦላህ የሕይወት ገፅታዎች አሉ።

<u>በጨቋኞቹ እጆች የተቀበለው መከራ</u>
<u>በሰዎች ልብና አዕምሮ ላይ ያሰረጸው ኃይልና መልካም ተፅዕኖ ነው</u>

የባሃኦላህ መከራ የጀመረው የእግዚአብሔርን እምነት ለማወጅ እንደተነሳ ወዲያው ነበር። ሕይወቱን ሁሉ የኖረው በግዞት፥በእስራትና በጭቆና ነበር። መጀመሪያ በቴህራን ከተማ በሚገኝ ጨለማና ፀሐይ የማይደርስበት ጉድጓድ ውስጥ በሠንሰለት ታሰረ። ከአንዱ አገር ወደ ሌላው አገር አራት ጊዜ በግዞት ተንከራተተ፤ በመጨረሻም በኦቶማን ግዛት ውስጥ የእስር ከተማ ወደ ነበረችው እስራኤል አገር አቆር ከተማ ተላከ። በዚህ ከተማ ስቃዩ ከመብዛቱ የተነሳ አቆርን "እጅግ በጣም ታላቁ እስር ቤት" ብሎ ጠራው። ከፅሑፎቹ በአንዱ ይህን እናነባለን፡ -

"... በዚህ ሩቅ ወህኒ ቤትም ስቃዬንና ግዞቴን አስታውስ፥ እንዲሁም የጠላቶች ሰይፎች ጭፍጨፋ ቢያዘንቡብህም... ልብህ እንዳያመነታ በፍቅሬ የፀናህ ሁን።"

# ባሃኦላህ የተቀዳጃቸው ድሎች

ሁለቱ ኃያላን መንግስታት፥ ማለትም የኢራን ንጉስና የኦቶማን ንጉሠ ነገስት፥ ባሃኦላህንና ትምህርቶቹን ለመቃወም ከፍተኛ ጥረት አደረጉ:: ነገር ግን የእውነት ብርሃን የሚጠፋ አይደለም:: ይህን እንደእሳት የሆነውን ብርሃን ለማጥፋት በላዩ ላይ የሚደፋ ውሃ ወደ ነዳጅነት ተለውጦ የበለጠ እሳቱን አፋፋመው:: እያደገ የሄደውን የባሃኦላህን ታዋቂነት ለማቆም ምንም ማድረግ አልተቻለም:: ባለሥልጣኖቹ የበለጠ ሩቅ ቦታ ባጋዙት ቁጥር ወደ ትምህርቶቹ የሚሳቡና ብርታቱንና ግርማውን የሚያውቁ ሰዎች ቁጥር እየበዛ ሄደ:: የማያቋርጥ ጭቆና ቢደርስበትም ከአርባ ዓመታት ለበለጠ ጊዜ ባሃኦላህ የእግዚአብሔርን ቃል መግለጽን ቀጠለ:: ወደ እዚህ ዓለምም እጅግ በጣም ከፍተኛ ፍቅርና መንፈሣዊ ኃይል ከማምጣቱ የተነሣ የእምነቱ ድል የተረጋገጠ ሆኗል::

# የባሃኦላህ ከዚ.ህ ዓለም መለየት

እ.ኤ.አ በ1892 ባሃኦላህ ከዚህ ዓለም ተለየ:: ባሃኢዎች በምድር ላይ እጅግ በጣም ቅዱስ ቦታ ነው የምንለው መካነ መቃብሩ እስራኤል አገር በአቆር ከተማ አቅራቢያ ይገኛል::

ባሃኦላህ ስለደረሰበት መከራ እንደሚከተለው ጽፏል:-
"ጥንታዊው ውበት የሰው ልጅ ከእሥረኝነቱ ነፃ ይወጣ ዘንድ በብረት ሠንሰለት ለመታሠር ፈቀደ ፤ መላው ዓለም እውነተኛ ነፃነት ይቀዳጅ ዘንድ በዚህ እጅግ በጣም ብርቱ ምሽግ ውስጥ እስረኛ መሆንን ተቀበለ:: የምድር ሕዝቦች ሁሉ ዘላቂ ፍስሐን ይቀዳጁ ፤ በደስታም የተመሉ ይሆኑ ዘንድ የኃዘንን ጽዋ እስከ መጨረሻው ጠብታ ጨለጠ:: ይህ ከሩኅሩኁ÷ ከእጅግ በጣም መሐሪው÷ ጌታችሁ ምህረት የተነሣ ነው:: በአምላክ አንድነት አማኞች ሆይ÷ እናንተ ትከበሩ ዘንድ መዋረድን÷ እናንተ ትበለጽጉና ታብቡ ዘንድ÷ ብዙ ከባድ መከራዎችን ተቀብለናል:: እርሱን÷ መላውን ዓለም በአዲስ ይገነባ ዘንድ የመጣውን÷ እነዚያ ከእግዚአብሔር ጋር ራሳቸውን ያወዳደሩት ከከተሞች እጅግ በጣም ባድማ በሆነው ከተማ ውስጥ እነዲኖር እንዴት እንዳስገደዱት ተመልከቱ!"

# የባብ ደረጃ

ባብ ከባሃኢ እምነት ማዕከላዊ ስብዕናዎች አንዱ ነው፡፡ በየዘመኑ የእግዚአብሔር ክስተት ከመገለጹ በፊት÷ ስለእርሱ መምጣት የሚያውጅ እግዚአብሔር ይልካል፡፡ ለምሳሌ ክርስቶስ ራሱን ከመግለጹ በፊት መጥምቁ ዮሐንስ ለሕዝቡ የመሲሁ መምጫ መድረሱን ያውጅ ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሁናቴ ፤ ባሃኦላህ ተልዕኮውን ከማወጁ ብዙ ዓመታት አስቀድሞ የእርሱን መምጣት የሚያበስር መልዕክተኛ እግዚአብሔር ልኮ ነበር፡፡ ይህ ታላቅ መልዕክተኛ ባብ ይባላል፡፡ “ባብ” ማለት በር ማለት ነው፡፡ ባብ በዚህ ዘመን እግዚአብሔርን ለማወቅና ለሰው ዘርም ሁሉ የአዲስ ዘመን በር ነው፡፡ አዲስ የእግዚአብሔር ክስተት ሊገለጽ መሆኑን ለስድስት ዓመታት ሳያቋርጥ አስተማረ÷ መንገዱንም አዘጋጀ፡፡ ተስፋ የተገባለት አዲስ ዘመን ጎህ እየቀደደ መሆኑን ለህዝቡ ሁሉ አበሰረ፡፡ በቅርብ ጊዜ እግዚአብሔር የሚከስተውን ለማወቅ ይችሉ ዘንድ ልቦቻቸውን ከምድራዊ ከንቱነት እንዲያፀዱ ለሕዝቡ ጥሪ አቀረበ፡፡

# የባብ ሕይወት

የባብን መልዕክት በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ተቀበሉት፤ ትምህርቶቹንም መከተል ጀመሩ:: ነገር ግን የኢራን መንግስትና ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸው ካህናት በእርሱ ላይ ተነሱበት:: ተከታዮቹ ጭቆና ደረሰባቸው÷ ብዙዎቹም ተገደሉ:: ባብ በሠላሳ አንድ ዓመቱ በመንግስት ትዕዛዝ አደባባይ ላይ ተሰቅሎ በ 750 ወታደሮች ተኩስ ሰማዕትነትን ተቀበለ::

የባብ ቃላት ምን ያህል ኃያል መሆናቸውን ለመረዳት እንድንችል ከገለጻቸው ጸሎቶች መካከል ሁለቱን ጸሎቶች እንይ::

“ከእግዚአብሔር በስተቀር ችግርን የሚያስወግድ አለ ወይ? በል÷ ለእግዚ አብሔር ምስጋና ይድረሰው! እርሱ አምላክ ነው! ሁሉም አገልጋዩቹ ናቸው፤ ሁሉም በትዕዛዙ ይኖራሉ::”

“በል፡- እግዚአብሔር ሁሉን ነገሮች ከሁሉም በላይ ያረካል፤ በሰማይና በምድር ከእግዚአብሔር በስተቀር የሚያረካ የለም፤ በእውነቱ እርሱ በራሱ አዋቂው፤ ሕይወት ሰጪው÷ ምንም የማይሳነው ነው::”

# የባብ መካነ-መቃብር

ከሰማዕትነቱ በኋላ የባብ አስከሬን ከከተማው መግቢያ በሮች ውጪ ተጣለ። ከዚያም በተከታዮቹ ተወስዶ ከቦታ ወደ ቦታ ተዘዋወረ። ከእምነቱ ጠላቶች ሁል ጊዜ እየደበቁት ነበር። በመጨረሻም በቅድስት አገር (እስራኤል) ወደሚገኘው ቀርሜሎስ ተራራ ተወሰደ።

ባሃኦላህ ስለ ቀርሜሎስ ተራራ የሚከተለውን ገልጿል፡-
"ቀርሜሎስ ሆይ! ወደ ጽዮን ጥሪ አቅርቢና÷ እርሱ ከሟች ዓይኖች ተደብቆ የነበረው መጥቷል! የሚለውን ሐሴት የተመላበትን ዜና አብስሪ። የእርሱ ሁሉን ድል አድራጊ ሉዓላዊነት ተከስቷል÷ ሁሉን የሚያቅፈው የእርሱ አንጸባራቂ ውበት ተገልጿል። እንዳታመነቺ ወይም እንዳትቆሚ ተጠንቀቂ። ፈጥነሽ ወጥተሽ÷ የእግዚአብሔር ምርጦች÷ ልበ ንጹሃንና እጅግ በጣም የተከበሩት የመላእክት ኅብረት በማምለክ በዞሩዋት÷ ከገነት የወረደች ካባ በሆነችው በአምላክ ከተማ ዙሪያ ዙሪ። አቤቱ ስለዚህ ግልጸት የሲና ልብ የተሳበበት፤ በስሙም የሚነደው ቁጥቋጦ÷ 'የምድርና የሰማይ መንግሥታት÷ የጌቶች ጌታ የሆነው የእግዚአብሔር ናቸው' በማለት ስለሚጣራው ስለዚህ ግልጸት የምስራች ዜና በምድር ገጽ ላይ ለሚገኘው ለእያንዳንዱ ሥፍራ ለማብሰር÷ ለእያንዳንዱም ከተሞቿ ለማዳረስ ምንኛ እጓጓለሁ።"

# የባሃኡላህ ቃል-ኪዳን

በሁሉም ሌሎች ሃይማኖቶች ክስተቱ ካለፈ በኋላ ተከታዮቹ በብዙ ነገሮች ላይ ሲጨቃጨቁ ኖረዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ሃይማኖታቸውን ወደ ብዙ ቅርንጫፎች ከፋፍለውታል፡፡ ባሃኡላህ እምነቱን ከእንደዚህ ዓይነት መከፋፈል ጠብቆታል፡፡ ይህንንም ያደረገው ልዩ በሆነ ኃይል ማለትም በቃል-ኪዳኑ ኃይል እምነቱን በማስጠበቅ ነው፡፡ ከዚህ ዓለም ከመለየቱ በፊት በጽሑፍና ግልፅ በሆነ ቋንቋ ከእርሱ በኋላ ባሃኢዎች ወደ አብዱል-ባሃ በመዞር የእርሱን መመሪያ መከተል እንዳለባቸው ገልጾ ነበር፡፡ ስለሆነም የበኩር ልጁን አብዱል-ባሃ ብቸኛው የቃሉ ተርጓሚና የቃል-ኪዳኑ ማዕከል አደረገው፡፡ ያሳደገው ባሃኡላህ ራሱ ነበር፡፡ ልጅ በነበረበት ጊዜ እንኳን የአባቱን ደረጃ አውቆ ነበር፡፡ የአባቱን ስቃዮችም ተካፍሎአል፡፡

# የአብዱል-ባሃ ሕይወት

አብዱል-ባሃ የተወለደው ባብ እ.ኤ.አ በ1844 ተልዕኮውን ባወጀበት ምሽት ነበር። አብዱል-ባሃ በዚህ ምድር ላይ ለ77 ዓመታት ኖረ፡፡ እ.ኤ.አ በ1921 በኖቬምበር ወር ከዚህ ዓለም ተለየ፡፡ ትክክለኛ የባሃኢ ባህሪያቶች እንዲኖረው አድርጎ ያስተማረው ባሃኦላህ እራሱ ነበር፡፡ አብዱል-ባሃ ለሰው ልጅ የተሰጠ እጅግ በጣም ብርቅ የሆነ ሥጦታ ነው፡፡ ባሃኦላህ የሰው ልጅ በሙሉ እንዲቀዳጅ የሚፈልጋቸውን እንደ ፍቅር÷ ለጋስነት÷ ትዕግስትና የመሳሰሉ መንፈሣዊ ባህሪያት ለማዳበርም ፍፁም የሆነ አርአያ አብዱል-ባሃ ነው፡፡

ባሃኦላህ ከዚህ ዓለም ከተለየ በኋላ የባሃኢ ማኅበረሰብን የመምራት ሃላፊነት በእርሱ ትከሻ ላይ አረፈ፡፡ እምነቱ በምስራቅና በምዕራብ እንዲሠራጭ በቀንና በማታ ይለፋ ነበር፡፡ በሁሉም ቦታ ላሉ ግለሰቦችና ቡድኖች ብዙ ሺ መልዕክቶችን ጽፏል፡፡ የአባቱን ትምህርቶችንም አብራርቷል፡፡ የአብዱል-ባሃ ማብራሪያዎች የባሃኢ እምነት ጽሑፎች አስፈላጊ አካል ናቸው፡፡

በዓለም ዙሪያ ያሉ ባሃኢዎች የባሃኢነትን ሕይወት ለመኖርና አዲሱን መንፈሳዊ ሥልጣኔን ለመገንባት በሚያደርጉት ጥረት አንድነታቸውን ጠብቀው መኖር የቻሉት የባሃኦላህ ቃል-ኪዳን ማዕከል በሆነው በአብዱል-ባሃ ላይ በማተኮር ነው፡፡

# የባሃኢ ህጎች

እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ግልጸት የሰው ልጅ በትክክለኛው መንገድ እንዲመራ ሕግጋትና ትዕዛዛትን ያመጣል:: ከእነኚህ ሕግጋትና ትዕዛዛት አንዳንዶቹ ዘለዓለማዊ ናቸው:: ሌሎች ደግሞ የሰው ልጅ ባደገና በተሻሻለ ቁጥር ይለወጣሉ:: የባሃኢ እምነት ሕግጋት የ “አድርጉ” እና “የአታድርጉ” ዝርዝሮች ናቸው ብለን ማሰብ እንደሌለብን ባሃኦላህ ያስተምረናል:: ባሃኦላህ እንደሚነግረን የእርሱ ሕግጋት “በአገልጋዮቼ መካከል የፍቅራዊ እንክብካቤ ብርሃኖችና ለፍጡራኔ የምህረቴ ቁልፎች” ናቸው:: “ትዕዛዛቴን ለውበቴ ፍቅር ስትሉ ጠብቁአቸው::” ብሎናል::

Ann's A5 texts.indd 17 2/3/2008 4:11:24 AM

# ፀሎት

የሰው ልጅ በምድር ላይ ሲኖር በየቀኑ ምግብ መመገብ አለበት:: ይህ ለሰው አካል አስፈላጊ ነው:: ካልበላን ታመን ቀስ በቀስ እስከ መሞት ልንደርስ እንችላለን:: ስለዚህ መብላት በምድራዊ ኑሯችን መታዘዝ ያለብን ሕግ ነው::

በተመሳሳይ መንገድ ከባሃኦላህ ትዕዛዛት መካከል አንዱ በየቀኑ መጸለይ ነው:: እንደ አካላችን ሁሉ ነፍሳችንም ሁልጊዜ ምግብ ያስፈልጋታል:: ጸሎት ለመንፈሳዊ ዕድገታችን ምግብ ነው:: ጸሎት ስናደርግ እግዚአብሔር ሕይወታችንና ኑሮአችንን ይባርክልናል:: በባብ፥ በባሃኦላህና በአብዱል-ባሃ የተገለጹ ብዙ ልብን የሚማርኩ ጸሎቶች አሉ:: እነኚህን ጸሎቶች ለብቻችን ወይንም በጋራ ሁነን መጸለይ እንችላለን::

ጸሎት "ከአምላክ ጋር ማውጋት ነው::" የእውነተኛ አፍቃሪ ብርቱ ፍላጎት ከሚያፈቅረው ሰው አለመለየትና ከእርሱም ጋር ማውጋት ነው:: ስለዚህ አንድ ባሃኢ ለአምላክ ላለው ፍቅር ምልክት ይሆን ዘንድ ከእርሱ ጋር መነጋገርን በሌላ አገላለጽ በየቀኑ መጸለይን ይመኛል::

# የግዴታ ፀሎት

ከግዴታ ጸሎቶች አንዱን በየቀኑ በቀትርና በፀሐይ መጥለቅ መካከል ባለው ጊዜ ባሃኢዎች ይጸልዩታል:: እንዲህ ይላል:-

“አምላኬ ሆይ÷ አንተን እንዳውቅና እንድሰግድልህ እንደፈጠርከኝ እመሰክራለሁ:: በዚህች ሰዓት የእኔን ደካማነት ያንተን ኃያልነት÷ የኔን ምስኪንነትና ያንተን ሃብታምነት አረጋግጣለሁ:: ከአንተ በአደጋ ጊዜ ረዳት÷ በገዛ ራሱም ነዋሪ ከሆንከው በስተቀር ሌላ አምላክ የለም::”

# ሐሜትና ስም ማጥፋት

ባሃኡላህ ሐሜትና ስም ማጥፋትን ይከለክላል። ይህን ማጤን ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም አንድነት እንዳይኖረን ከሚያደርጉት እጅግ በጣም ታላላቅ ጠላቶች አንዱ ሐሜት ነው። የሚያሳዝነው ነገር የሌሎችን ሰዎች ስህተቶች በሌሉበት ማውራት በአብዛኞቹ ሰዎች መካከል በቀላሉ ሊቀር የማይችል ልምድ ሆኗል። እያንዳንዱ ሰው በሌሎች ሰዎች ጉድለቶች ላይ ሲያተኩርና እነኚህ ጉድለቶች ተደጋግመው ሲነገሩ እየጎሉ ይሄዳሉ። አብዱል-ባሃ የዚህን ተቃራኒ እንድናደርግ ይነግረናል። አንድ ሰው ላይ አሥር ጥሩ ባህሪያትና አንድ ጉድለት ብንመለከት በአሥሩ ላይ ማተኮር አለብን። እንዲያውም አንድ ሰው አስር መጥፎ ባህሪያትና አንድ ብቻ ጥሩ ባህሪ ቢኖረው በዚያ በአንዱ ባህሪ ላይ ማተኮር አለብን።

# እርኩስ ነገር አትስማ ፤ እርኩስ ነገር አትናገር

የዙፋኔ ጓደኛ ሆይ!

እርኩስ ነገር አትስማ፤ እርኩስ ነገር አትመልከት፤ ራስህን አታዋርድ፤ እንዲሁም አትዘን፥ አታልቅስ። እርኩስ ነገር አትናገር፥ በአንተ ላይ ሲነገር እንዳትሰማ፤ የሌሎችን ስህተት አታጉላ፥ የራስህ አይሎ እንዳይታይብህ የማንንም ውርደት አትመኝ፥ የራስህ ውርደት እንዳይገለጽብህ እንግዲህ በነጻነትና በእርጋታ፥ ይህንን ሟች አካል ጥለህ ወደ ረቂቋ ገነት ተመልሰህ በማይጠፋው መንግስት ለዘላለም ትኖር ዘንድ፥ ከመቅጽበት ከሚያልፍ ጊዜ ያነሱትን የሕይወትህን ቀኖች፥ በአእምሮህ እንከን አልባ፥ በልብህ ያልጎደፍህ፥ በሃሳብህ ንፁሕ፥ በተፈጥሮህም የተቀደስክ ሆነህ ኑር።

# አልኮል መጠጥና የአደንዛዥ ዕጽ መጠቀም መከልከል

አልኮል መጠጥ መጠጣት በዛሬው ጊዜ በዓለም ውስጥ ካሉት እጅግ በጣም ታላላቅ ማኅበራዊ ችግሮች አንዱ ነው፡፡ አላስፈላጊ የሆነ ኃይልን የመጠቀምና ጤናማ የሆነ የቤተሰብ ኑሮን ለማፍረስ ብዙ ጊዜ ምክንያት የሚሆነው አልኮል መጠጥ ነው፡፡ እግዚአብሔር ከእንስሶች የሚለዩንን ልዩ ስጦታዎችን ሰጥቶናል ይህም ሰጦታ የማገናዘብና የማሰብ ችሎታ ነው፡፡ አልኮል ስንጠጣ ይህን ችሎታችንን እናጣና እንደ እንስሳ እንሆናለን አንዳንዴ እንዳውም ወዳጆቻችንንም ልንገድል እንችላለን፡፡ አልኮል መጠጣት ሰዎች የሚያሳፍሩ ሥራዎችን እንዲሠሩ ያደርጋቸዋል፤ የተፈጠርነው ግን ክቡር ተደርገን ነው፡፡ ባሃኦላህ እንዲህ ይላል፡-

የመንፈስ ልጅ ሆይ!
...ክቡር አደረግሁህ÷ ለምን ራስህን ታዋርዳለህ? ከዕውቀት ምንጭ ሕይወት ሰጠሁህ÷ ለምን ከእኔ በቀር ከሌላ የዕውቀት ብርሃን ትሻለህ? ከፍቅር አፈር ሠራሁህ÷ እንዴት ራስህን ከሌላ ጋር ታወዳጃለህ? ...

# ፆ ም

ፆም:- አንድን ሃይማኖት እንደምሰሶ ሆነው ከሚደግፉት ዋና ሕጎች አንዱ ነው። የጾም ወቅት መላ ትኩረታችንን ወደ አምላክ ለማድረግ አስታዋሽ ነው። ባሃኦላህና አብዱል-ባሃ ስለ ጾም ዓላማ ሲያስተምሩን:-

ለተወሰነ ወቅት እንድትጾሙ አዘናችኋል።

ጾም ከሥጋዊ ፍላጎት የመጠበቅ ምልክት ነው። ጾም ምሳሌና አስታዋሽ ነው። ይህም ማለት ሰው ከምግብ ፍላጎት እንደሚከለከል ሁሉ ከግላዊ ምኞትና ፍላጎትም መጠበቅ ይገባዋል ማለት ነው።

የጾም ወቅት ... በመሠረቱ የማሰላሰልና የጸሎት 'የመንፈሳዊ ተሃድሶና አማኙ በውስጣዊ ሕይወቱ ውስጥ መሻሻል ለማሳየት የሚሞክርበት' በነፍሱ ውስጥ ያሉትን ድብቅ ኃይላት የሚያድስበትና የሚያነቃቃበት ወቅት ነው። ስለሆነም አስፈላጊነቱና ምክንያቱ በባህሪው መንፈሳዊ ነው። ጾም... ከራስ ወዳድነትና ከሥጋዊ ፍላጎቶች መወገድ ነው።

ጾምና የግዴታ ፀሎት የተገለጸውን የእግዚአብሔር ሕግ የሚደግፉ ሁለት ምሰሶች ናቸው። ባሃኦላህ ከጽሑፎቹ በአንዱ ውስጥ የግዴታ ፀሎትንና የጾምን ሕግጋት የገለጸው አማኞች በእነርሱ አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ ለማድረግ መሆኑን ያረጋግጣል።

# ልጆችን ማስተማር

ወላጆችና ኅብረተሰብ ልጆችን የማስተማር ግዴታ አለባቸው:: ይህ ከባሃኡላህ ትምህርቶችና ትዕዛዛት አንዱ ነው:: ከአብዱል-ባሃ ጽሑፎች የሚከተለውን እናገኛለን:-

"... ስለዚህ የእግዚአብሔር ተወዳጆችና የምህረተኛው ሴት አገልጋዮች ልጆቻቸውን ሕይወታቸውን በመስጠትና በሙሉ ልባቸው ማሰልጠንና ከፅድቅናና ከፍፁምነት የትምህርት ገበታ ማስተማር አለባቸው:: በዚህ ጉዳይ ቸልተኛ (ልል) መሆን የለባቸውም፤ ውጤታማነት የጎደላቸው መሆን የለባቸውም:: በእርግጥ አንድ ጨቅላ ሕፃን ደንቆሮ (ማሐይም) ሆኖ እንዲያድግ ከማድረግ ይልቅ ጭራሹኑ ባይኖር ይሻለው ነበር:: ምክንያቱም ያ ክፋት የማያውቅ ሕፃን በቀጣይ ሕይወቱ በእግዚአብሔር ፊት በኃላፊነት የሚያስጠይቁትን÷ በሕዝቡ የሚያስወቅሱትና ተቀባይነት የሚያሳጡት ቁጥር የሌላቸው ጉድለቶች ያሰቃዩታልና:: ይህ ምን ዓይነት የከፋ ኃጢአት ነው÷ ምን ዓይነት ግድፈትስ ነው!

የእግዚአብሔር ተወዳጆችና የመሐሪው ሴት አገልጋዮች የመጀመሪያው ኃላፊነት ይህ ነው:- በተቻለ መንገድ ሁሉ ሁለቱንም ፆታዎች÷ ወንዶችንና ሴቶችን ... ለማስተማር መጣር አለባቸው÷ በመሐከላቸው ምንም ዓይነት ልዩነት የለም:: የሁለቱም ድንቁርና ያስወቅሳል በሁለቱም በኩል ቸልተኝነት አስወቃሽ ነው:: እነኛ የሚያውቁና የማያውቁ እኩል ናቸው?"

# የባሃኢ እምነት ዓላማ

የባሃኢ እምነት የጥሩ አስተሳሰቦች ስብስብ ሳይሆን እራሱን የቻለ ሃይማኖት ነው። የባሃኢ ሃይማኖት በደንብ የተደራጀ ሥርዓት ያለው ነው። ዓላማውም የመላው የሰው ዘር አንድነት ነው። ስለሆነም የባሃኢዎች ሥራ ለሰው ዘር አንድነትና ሰላም መመስረት መሥራት ነው።

በዚህ ሥራ ሦስት ተሳታፊዎች እንዳሉ የባሃኢ ከፍተኛ ተቋም የሆነው ዓለም ዓቀፍ ቤተ-ፍትህ ይነግረናል። እነርሱም፡-

- ግለሰቡ
- ማኅበረሰቡና
- የእምነቱ ተቋማት ናቸው።

እያንዳንዱ ተሳታፊ በጣም ጠቀሚ ሚና አለው።

## ግለሠቡ

በቃል-ኪዳኑ መጽናት÷ በቀን ተቀን ሕይወቱ ወይንም ሕይወቷ በባሃኦላህ ትምህርቶች መሠረት ለመመራትና የሰውን ልጅ ለማገልገል ጥረት ማድረግ የግለሰቡ ሃላፊነት ነው:: በዋነኛነትም ሕይወት በሞት እንደማያበቃና አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ዘለዓለማዊ እንደሆነ ሁልጊዜ ማስታወስ አለበት::

ከሞት በኋላ ነፍስ ነፃ ትሆናለች:: ወደ እግዚአብሔር የምታደርገውም ዕድገት ለዘለዓለም ይቀጥላል:: እዚህ ያለው ሕይወታችን በእናቱ ማህጸን ካለ ሕፃን ሕይወት ጋር በጣም ይመሳሰላል:: ለዘጠኝ ወራት ያህል የሕፃኑ ዓይኖች÷ ጆሮዎች÷ እጆችና ሌሎች የአካል ክፍሎች በማህጸን ውስጥ ያድጋሉ:: እነኚህን የአካል ክፍሎች ከተወለደ በኋላ በዚህኛው ዓለም ይጠቀምባቸዋል:: በተመሳሳይ መንገድ ለሚቀጥለው የእግዚአብሔር ዓለም የሚያስፈልጉንን መንፈሣዊ አካላት (መንፈሣዊ ባሕሪያት) እዚህ ሆነን ማዳበር አለብን:: በእርግጥ ይህን ዓላማችንን በሃሳብ ብቻ ልናሳካ አንችልም:: መንፈሣዊ ዕድገት ለመጎናጸፍ መጣር አለብን÷ ሰብዓዊ ፍጡሮችን (ሰዎችን) ማገልገልና ያገኘነውን ዕውቀት ማካፈል አለብን::

# ከሞት በኋላ ህይወት

ከሞት በኋላ ወደ እግዚአብሔር መቅረብን መቀዳጀት እንችል ዘንድ አሁን በምንኖርበት ዓለም መንፈሳዊ ባህሪያቶችን በማዳበር ነፍሳችንን ማዘጋጀት እንዳለብን ባሃኢዎች ያምናሉ::

አንድ በጎጆ ውስጥ ትኖር የነበረች ወፍን ለምሳሌ ብንወስድ:: ዕድገትን ታገኝ ዘንድ ትበላለች ትጠጣለች:: በድንገት ይህ ጎጆዋ ፈረሰና ወፏ እንደልቧ በነፃነት መብረር ቻለች:: ክንፎችዋ ከጠነከሩ ከዚህ በፊት አይታው ወደማታውቀው ቦታ መብረር ትችላለች:: እኛም ልክ እንደዚሁ ነንና ሥጋችን ልክ በስተመጨረሻ እንደፈረሰው የወፏ ጎጆ ነው:: በምንሞትበት ጊዜ ሥጋችን እዚሁ የሚቀርና የሚበሰብስ ሲሆን ነፍሳችን ግን ወደ መንፈሣዊው ዓለም ትሄዳለች:: የሚወደውን ሲያጣ አንድ ሰው ተፈጥሮአዊ የሃዘን ስሜት ሊሰማው ይችላል፤ ነገር ግን ሞት ቅጣት አለመሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል:: አንድ ሰው እግዚአብሔርን ሲያውቅና ትምህርቶቹን ሲከተል ነፍሱ ከሥጋው ከተለየች በኋላ ወደ እግዚአብሔር ትቀርባለች:: በአምላክ ትዕዛዛት መሠረት ካልኖረ ግን በእርግጠኝነት ከእግዚአብሔር ይርቃል::

አንድ ሰው ወደ እግዚአብሔር ሲቀርብ በገነት ውስጥ ይሆናል፤ ከእርሱ ከራቀ ግን በጨለማና በጥልቅ ገሃነም ውስጥ ይሆናል::

# ማኅበረሰቡ

ሰው የተፈጠረው ብቻውን እንዲኖር አይደለም፤ በጋራ አብሮ ተባብሮ በማሕበረሰብ ደረጃ እንዲኖር እንጂ:: ስለሆነም በማኅበረሰቦች ውስጥ እንኖራለን፤ ለአዲሱ መንፈሳዊ ሥልጣኔም አብረን መሥራት አለብን:: የመጀመሪያው የባሃኢ ማሕበረሰብ ደረጃ የአንድ መንደርን ወይንም ከተማን ባሃኢዎች የሚያቅፈው የአካባቢ ማኅበረሰብ ነው:: እርስ በእርስ መተጋገዝን÷ አብሮ ማደግንና አንድ መሆንን የምንማረው በአካባቢ ማኅበረሰባችን ውስጥ ነው:: የአካባቢ ማኅበረሰብ አባላት ከመሆናችን በተጨማሪ የብሔራዊ ማኅበረሰብ ከዚያም በመቀጠል በዓለም ዙሪያ ያለው የባሃኢ ማኅበረሰብ አባላት ነን:: ይህ ዓለም-አቀፍ የባሃኢ ማኅበረሰብ ሳያቋርጥ እየተስፋፋ ነው:: እንዲሁም ከሁሉም ሃይማኖቶች÷ ዘሮችና ብሔሮች ሰዎችን እየሳበ ይገኛል::

Ann's A5 texts.indd 28 2/3/2008 4:11:25 AM

# የባሃኢ ተቋማት

ባለፉት ዘመናት የእግዚአብሔር ግልጸቶች ተከታዮቻቸው እንዴት መደራጀት እንዳለባቸው ብዙም አልተናገሩም:: ተከታዮቻቸውም ራሳቸውን እንዴት ማስተዳደር እንዳለባቸው መንገዱን እራሳቸው ማግኘት ነበረባቸው:: ነገር ግን በባሃኢ እምነት ባሃኦላህ የአስተዳደር ሥርዓት ደንግጓል:: ይኸውም ምን ዓይነት ተቋማት መመሥረት እንዳለብን፤ እንዴት እንደሚሠሩና የሰው ልጅ እንዴት በእነርሱ መተዳደር እንዳለበት ነግሮናል ማለት ነው::

ለባሃኢዎች ከፍተኛው ተቋም ዓለም-አቀፍ ቤተ-ፍትህ ነው:: በእያንዳንዱ አገር ደግሞ በዓመት አንድ ጊዜ ባሃኢዎች ብሔራዊ መንፈሣዊ ጉባዔን እንዲሁም በእያንዳንዱ አካበቢ የአካበቢ መንፈሣዊ ጉባዔን ይመርጣሉ:: የማኅበረሰቡን ጉዳዮች የሚመራና የግለሰቡ አማኞችን ደህንነት የሚጠብቅም የአካባቢ መንፈሣዊ ጉባዔ ነው:: የአካባቢ መንፈሣዊ ጉባዔ 9 አባላት አሉት:: አባላቱ የሚመረጡት በማኅበረሰቡ ውስጥ ባሉት ጎልማሳ አማኞች (21 ዓመትና ከዚያ በላይ) ሲሆን ምርጫው የጸሎት መንፈስ በሰፈነበትና በሚስጥር ይደረጋል:: መንፈሣዊ ጉባዔዎች እጅግ በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ናቸው:: በእነርሱ አማካኝነት የግለሰብና የማሕበረሰብ ጉዳዮችን እንዴት ማስተዳደርና እንዲሁም አዲስ ሥርዓትን እንዴት መመሥረት እንደሚቻል እንማራለን:: ይህ አዲስ ሥርዓት የባሃኦላህ ዓለም-አቀፍ ሥርዓት ተብሎ ይታወቃል::

# የባሃኢ እምነትን እንዴት መቀበል ይቻላል?

በዚህ አጭር ጽሑፍ ለመዳሰስ የሞከርነው የባሃኢ እምነትን ዓላማና ተግባር ነው።

ባሃኢ ለመሆን አንድ ልዩ በሆነ ሥነ-ሥርዓት ውስጥ ማለፍ አይጠበቅብንም። አስፈላጊ የሆነው ነገር ቢኖር አንድ ሰው ከልቡ ባሃኦላህ ለዚህ ዘመን የተላከ የእግዚአብሔር ግልጸት እንደሆነ ማመንና የእግዚአብሔር ቃላትና መመሪያ በእርሱ በኩል እንደተገለጹ መቀበል ነው። አንድ ባሃኢ ባሃኦላህን ከተቀበለ በኋላ በንቃት ትምህርቶቹን በሕይወቱ ላይ ተግባራዊ ማድረግ መጀመርና በየቀኑ ስለ ባሃኢ እምነት ያለውን ግንዛቤ ለመጨመር መጣር አለበት።

# የመንፈሣዊ ባህሪያትን ለማዳበር ፀሎት

አምላክ ሆይ! መንፈሴን አድስልኝ፣ አስደስትልኝም። ልቤን አንፃልኝ። አእምሮዬን አብራልኝ። ጉዳዮቼን ሁሉ በአንተ ላይ ጥዬአለሁ። አንተ መሪዬና መሸሻዬ ነህ። ከእንግዲህ ወዲያ የተከፋሁና ኃዘንተኛ አልሆንም፣ ደስተኛና በሐሴት የተመላሁ እሆናለሁ። አምላክ ሆይ፣ ከእንግዲህ ወዲያ በሥጋት ውስጥ አልዋኝም፣ ችግርም እንዲያስጨንቀኝ መንገድ አልሰጥም። ደስ በማያሰኝ የህይወት ነገር ውስጥ አልኖርም። አምላክ ሆይ! አንተ ከራሴ ይልቅ ለኔ ትራራልኛለህ። ጌታ ሆይ፣ ራሴን ለአንተ አደራ ሰጥቻለሁ።